በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
መስተዳድር ም/ቤት
The Peoples' National Regional State
Council of Gambella

ቁጥር 002/2968/መ4/2
ቀን 19/05/07

በ.ኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳዩ ሚኒስትር

ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳ/ጀኒራል

<u>አ/አበባ</u>

ጉዳ፡- **<u>በውጭ ሀገር የሚደራጀ የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የሞደል ቅጾች ስለመላክ፡-</u>**

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በመኖሪያ ቤት ለሚደረጁ የህብረት ሥራ ማህበራት የሞደል መስተዳደሪያ ደንብና ቅጾች እንዲንልክ መጠየቃችን ይታወቃል፡፡

ስለሆነም የሞዴል መስተዳደሪያ ደንብና ቅጾች አንድ ጥራዝ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አደርገን መላካችንን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

‹‹ከሠላምታ ጋር››

አቃርፋ ሙስጠፋ ሊኪስ
Akuda Mustefa Likiso
ም/ርዕስ መስተዳድር
Vice President

The Peoples' National Regional State Council of Gambella

<u>እንዲያውቁት</u>

- ለክቡር ርዕሰ መስተዳድር

<u>ግልባጭ</u>

- ለዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለርዕስ መስ/ጽ/ቤትና ካ/ጉዳዮች

<u>ጋምቤላ</u>

# በመመሪያ ቁጥር 1/2007 መሠረት ለሚደራጁ

# በውጪ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ

የመኖ/ቤ/ል/የመን/ህ/ከ/ ዋና የስራ ሂደት

ታህሳስ /2007

ጋምቤላ

The Peoples' National/ Regional State Council of Gambella

# <u>በውጪ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ</u>

## አንቀጽ 1፡ <u>ስለኅብረት ሥራ ማህበሩ መቋቋም</u>

የኅብረት ሥራ ማህበሩ በኢፌድሪ(በክልል)በህብረት ሥራ አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 9 መሠረት ተቋቁሞ በአንቀጽ 11 ድንጋጌ መሠረት ይህ መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል።

## አንቀጽ 2. <u>የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስያሜ</u>

የኅብረት ሥራ ማህበሩ የ................................................ የመኖሪያ ቤት ኃላፊነቱ የተወሰነ የኅብረት ሥራ ማህበር የሚል ስያሜ ይኖረዋል።

## አንቀጽ 3. <u>የኅብረት ሥራ ማህበሩ አድራሻ</u>

3.1 ክፍለ ከተማ ...........................

3.2 ወረዳ...............................

3.3 የቦታው ልዩ መጠሪያ .................

3.4 የቤት ቁጥር ........................

3.5 ስልክ ቁጥር ................

3.6 ፖ.ሣ.ቁ. .....................

## አንቀጽ 4. <u>የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓላማና ተግባር</u>

### 4.1 <u>ዓላማ</u>

4.1.1 ያለባቸውን የመኖሪያ ቤት ችግር በጋራ ጥረት ለመፍታት ፍቃደኛ የሆኑና ፍላጎት ያላቸውን አባላት በማሰባሰብ በህብረት ሥራ ማህበራት መርህ መሠረት እንዲደራጁ ማስቻል፣

4.1.2 የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት እውቀታቸውን ገንዘባቸውንና ጊዜያቸውን በማቀናጀት የመጠለያ ችግሮቻቸውን ሊፈቱ የሚችሉበትን አማራጭ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣

4.1.3 የኅብረት ሥራ ንድፈ ሃሳብ ዓላማና ተግባር በአባላቶቹ አመለካከት ውስጥ ሰርፆ እንዲገባና ወደ ተግባር እንዲለወጥ ማስቻል፣

4.1.4 የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በጋራ ሕንፃ የመጠለያና የአካባቢ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ አርአያነት ያለው ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፣

4.1.5 የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት እንዲያዳብሩ በማድረግ እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱና እንዲተጋገዙ ማስቻል፣